የሰ/መ/ቁ. 30947

ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

**አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽ ኮርፖሬሽን ቀረበ**

**ተጠሪ፡- አቶ ሲሳይ ጥላሁን ቀረበ**

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

**ፍ ር ድ**

በጉዳዩ ላይ ክርክር የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ሐምሌ 20 ቀን 1997 ዓ.ም በአዘጋጀው የክስ ማመልከቻ ተጠሪው ከአመልካች ጋር መጋቢት 20 ቀን 1997 ዓ.ም ባደረገው የቴሌፎን ደንበኝነት ውልና ተጨማሪ ሲ.ዲ.ኤ.ም.ኤ ደብልዩ.ኤል.ኤል ውል መሰረት እንዲጠቀምበት በተሰጠው ቁጥር 2512569 በሆነ ስልክ መስመር በግንቦት 1997 ዓ.ም ላገኘው አገልግሎት መክፈል የሚገባውን ብር 85,032 (ሰማንያ አምስት ሺ ሰላሳ ሁለት) የአገልግሎት ሒሳብ አለመክፈሉን በዚህ ምክንያትም ድርጅቱ አገልግሎቱን ማቋረጡን ገልጾ ተጠሪ ይህንን ሒሳብ እንዲከፍል እንዲወሰንበት ሲል ክስ አቅርቧል፡፡

ተጠሪውም ታህሳስ 3 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ በክሱ ቁጥሩ የተጠቀሰውን ስልክ በውል መረከቡን አምኖ በክሱ የተጠቀሰው ክፍያ እንዲከፍል ምንም አይነት ጥሪም ሆነ ማስታወቂያ እንዳልደረሰው ስልኩንም ከ18 ቀን ባልበለጠ ጊዜ እንደተጠቀመበትና ክፍያው የተጋነነ መሆኑን በመጥቀስ ክሱ ውድቅ እንዲደረግለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከውላቸው ጋር በማገናዘብ መዝገቡን ከመረመረ በኋላ ከሳሽ ያቀረበው የውል ሰነድ አንቀጽ 11 የሚከፈለው ገንዘብና



የሚከፈልበት ጊዜ ተጠቅሶ ለተከራዩ እንደሚቀርብ ስለሚደነግግ ከሣሽ ይህን ማስታወቂያ ወይም ጥሪ ሳያቀርብለት እንዲከፍለው ክስ ማቅረቡ ተቀባይነት የለውም፡፡ በውሉ በስልኩ የተገለገለው ደንበኛ ማስታወቂያው በጊዜው ሳይደርሰው ቢቀር ደግሞ በመጠየቅያው ላይ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ እንዳይከፍል እንደሚያግደው ተብሎ የተደነገገውም ለተከሳሹ መብት የሚሰጥ እንጂ ተከሳሹ ማስታወቂያ ሳይደርሰው እንዲከፍል ግዴታ የሚጥልበት አይደለም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጐታል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/337 መሰረት በመሰረዝ መዝገቡን ዘግቶ መልሶታል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠውን ትእዛዝ በመቃወም ሲሆን ቅሬታውም ተጠሪው ከተሰጠው በራሪ ወረቀትና በ1997 ዓ.ም ነፃ የመረጃ ማዕከል አማካኝነት የተጠቀመበትን የአልግሎት ሒሳብ ስለሚያውቅ እንደዚሁም የውሉ አንቀጽ 11 ማስታወቂያ በማይሰጣቸው ሁኔታዎች ደንበኞች መክፈል የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች በግልጽ ባስቀመጡበት ሁኔታ ማስጠንቀቂያ የመስጠት አስፈላጊነት እንደዋና ምክንያት ሊቆጠር አይችልም፡፡ ተጠሪው አገልግሎት ማግኘቱን አምኗል፡፡ ክርክሩ የተጠየቀው ሒሳብ የተጋነነ ነው የሚል ነው፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሒሳቡ የተጋነነ መሆን ያለመሆኑን ተጣርቶ ክፍያው እንዲፈፀም መወሰን ሲገባው በውሉ አንቀጽ 11 ደንበኛው ማስታወቂያ ባይደርሰውም ክፍያውን ከመፈፀም አይድንም ተብሎ የተደነገገውን ያለአግባብ በመተርጐም ክሱን ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ያሳያል፡፡ ፌ/ከ/ፍ/ቤትም የቀረበለትን ይግባኝ መሰረዙ በአግባቡ አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ መጀመሪያ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት እንደገና አከራክሮ የቀረበውን ክስ ከማስረጃው ይዘትና ከሕግ አኳያ መርምሮ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ተብሎ እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡

አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ተጠሪው ቀርበው መልስ ባለመስጠታቸው ክርክሩ በሌሉበት እንዲታይ ታዟል፡፡ በመቀጠልም ተጠሪው

የስልክ ክፍያውን እንዲፈጽሙ ጥሪ ስላልተደረገላቸው ወይም ማስጠንቀቂያ ስላልተሰጣቸው ክፍያውን ሊፈጽሙ አይገባም ተብሎ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም ተጠሪው ስልኩን ሲገለገሉበት ከአመልካች ጋር ውል መስርተው ማስገባታቸውንና በዚሁ ስልክ መጠቀም መጀመራቸውን አልካዱም፡፡ የስልክ አገልግሎት ክፍያ እንድከፍል ጥሪ አልተደረገልኝም ማስታወቂያም አልደረሰኝም ማለታቸው ደግሞ ሒሳቡ ተመርምሮ ክፍያው ሲታወቅ እከፍላለሁ የሚል ሐሳብ ያላቸው መሆኑን እንጂ ማስታወቂያ ስላልደረሰኝ ክፍያውን አልከፍልም፣ እንድከፍልም ሕጉ አያስገድደኝ ማለታቸው ያለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የስልክ አገልግሎት ክፍያ በየወሩ የሚከናወን እንደመሆኑ መጠን ተጠሪው ክፍያውን በወቅቱ የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡ በውላቸው አንቀጽ 11 ስር የተደነገገውም ተጠሪው የክፍያ ማስታወቂያ ሣይደርሳቸውም የአገልግሎት ክፍያውን መክፈል እንደማይጠበቅባቸው የሚያሳይ እንጅ ተጠሪው ካልፈለጉ ላለመክፈል የሚችሉበት ምክንያት የሚሳጣቸው አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ክሱን ተቀብሎ ግራ ቀኙን በክፍያ መጠኑ አከራክሮ ተገቢውን መወሰን ሲገባው ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ የአመልካች የስልክ አገልግሎት ክፍያን የመሰብሰብ መብት የሚከለክል በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከ/ፍ/ቤትም ይግባኙን መሰረዙ አግባብ አይደለም፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 56323 የካቲት 16 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና ፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 46451 የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡



2. ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና በአገልግሎት ክፍያ መጠኑ ላይ ያለው ክርክርም አጣርቶ ተገቢውን ይወስን ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሰረት ጉዳዩን መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ እንዲቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ